# በእስላማዊ ፍርድ-ቤቶች ህብረት የተጠለለው የሽብርተኞች ቡድን ምን ያህል ተጠርጓል?

## እርምጃው የነተሎ ተሎ ቤት እንዳይሆን እሰጋለሁ!!

ከብስራት ከበደ
ሲያትል

መቸስ ጀግንነት የኢትዮጵያኖች ባህል መሆኑን ባልዘነጋም፣ በእስላማዊ ፍርድ-ቤቶች ስር ተጠልሎ የነበረው የሽብርተኞች ቡድን፡ አከርካሪው የመስበር ዘመቻ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መጠናቀቁ፡ የዓለማችን ህዝቦች ያስደነቀም፣ ያስደነገጠም ጉዳይ መሆኑ በማያጠራጥር አኳሃን ግልፅ ነው። በዚሁ አጋጣሚ፡ ወደር ለሌለው አኩሪና ጀግና የመከላከያ ሰራዊታችን ያለኝን አድናቆት በዚች ፅሁፌ ተተንትኖ የሚያልቅ ባይሆንም፣ ባጭሩ ግን ኮርቶ ላኮራን ጀግና የመከላከያ ሰራዊታችን፣ ዛሬም እንደ ትላንቱ እንኮራብሃለን ብቻ ማለቱ የሚሻል ይመስለኛል።

በአንድ ወጭፍ ሁለት ወፍ እንደሚባለው ሁሉ ሰላማችንንና ልማታችንን ለማደፍረስና ለማደናቀፍ የገሰገሱትን የሶማሌና የኤርትራው ጣዒር ሃዊሶች፡ በአንድ አለንጋ መገረፋቸው አጀብ የሚያሰኝ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ዳግም እንዳይመለሱ ትምህርት ሰጪ ግርፋት መሆኑን አንዱም ዋነኛውም አመላካች ነው።

ይሁን እንጂ፡ እኛ አፍሪካውያኖች በ21ኛው ክ/ዘመን ለሰላምና ለልማት፣ ለእድገትም፣ ለብልፅግናም ደፋ ቀና የምንልበት ዘመን እንጂ፣ እርስ በራሳችን ደም የምንፋሰስበት ዘመን መሆን ባልተገባ። ይሁንና፣ በማንኛውም ቦታና አጋጣሚ፣ አለመግባባቶች ሲከሰቱ፣ ወንበርና ጠረጴዛ የተሰራው ለመነጋገርና ችግሮችን በሁለትዮሽና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ስምምነት ለመድረስ መሰለኝ። ታድያ በጠረጴዛ ዙርያ ውይይትና ስምምነት አላምንበትም፣ የሚያዋጣኝ በአገሮችና በህዝቦች ቅዱስም ሆነ እርኩስ ጦርነት ማወጅ ብሎም ደም መፋሰስ እንዲከሰት ነው ላለ ሁሉ፣ መፍትሄው

እንደ ኑግና ተልባ መዶቆስ እንጂ ሌላ አማራጭ ሊኖር ባለመቻሉ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው። ያም ሆኖ የተወሰደው እርምጃ ባለንበት ዘመንና ስልጣኔ እንደመፍትሄ መወሰድ አልነበረበትም። ያ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ በአገራችንና በወገኖቻችን፣ አንዴ ቅዱስ ሌላው ደግሞ እርኩስ ጦርነት ሲያውጅብን፣ እጅና እግር አጣምሮ ማየት የሃገርንና የወገንን ህልውና አሳልፎ የሚሰጥ ዝምታ ስለሚሆን ዜግነታዊም ሆነ አገራዊ ሃላፊነት ለመወጣት ሳይወድ በግድ መንግስት ጦርነት ላይ መሳተፍ እንደሚገባው ብዙዎቻችን የምንገነዘበው ሃቅ መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ሃቁና እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፣ የኤርትራው ጣሂር በሶማሌው ጣሂር፣ የሶማሌው ጣሂር ደግሞ በኤርትራው ጣሂር በገናው ሰሞን የገና ጨዋታ ተያያዙት። የሁለቱም ጣሂሮች እርምጃ ተተኪ የሌለው (Precious life) የሰው ህይወት የገና መጫወቻ እንዲሆን አስከተለ። እንዲህ ነው እንግዲህ የሁለቱም ጣሂሮች ጭንቅላት የሚያስበው። ሁለቱም ጣሂሮች አመለካከታቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ነው። የኤርትራው ጣሂር በሶማሌው ጣህር ደም መቀለድ ይፈልጋል። የሶማሌው ጣሂር ደግሞ በኤርትራው ደም መነገድ ይፈልጋል። የሚያስደንቀውና የሚያስደስተው ጉዳይ ቢኖር ግን ሁለቱም ጣሂሮች በኢትዮጵያችን ላይ የጠነሰሱት እርኩስ ህልማቸው ሳይሳካላቸው ወደ ግብኣተ መሬት ገሰገሱ። የሚያሳዝነውና የሚያስደንግጠው ጉዳይ ደግሞ የኤርትራም ሆኑ የሶማሊያ ንፁሃን ዜጎች ባላመኑበትና ባላሰቡበት ወቅት የማይተካው ህይወታቸው አለፈ። ለእኔ እንደሚገባኝ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ማንንም አፍሪካዊ በከንቱ ሲያልፍ የሚደሰት ያለ አይመስለኝም። ዲክተተሮችና ጠባጫሪዎች የሚያስከትሉት ጉዳት ግን ካሁን በፊት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት "በኢትዮጵያችን ላይ የታወጀው ጦርነት ቅዱስ ወይስ እኩይ ብየ በፃፍኩት ፅሁፌ ላይ እንደጠቀስኩት ነው። አንዳንዶቻቸው የአፍሪካ ዲክተተሮች በሌሎች ዜጎች ደም ላይ መቀለድ ይቅርባቸው ብያለሁ። ያም ሆነ ይህ በዜጎች ህይወት ላይ መቀለድ እንደ ንግርት ሆኖ ተፈፀመ፣ መፈፀሙንም ለመላው የአለም ህዝቦች የሚያሳዝን ሆነ።

ምእራባውያን የልባቸው ሲናገሩ "መማር የዕድሜ ልክ ሂደት ነው ("Learning is a lifetime process") ይላሉ። ይህ ያልኩበት ምክንያት፣ ካለፉት ጦርነቶችና ደም መፋሰሶች የምንማረው ነገር አለ ወይ ለማለት ነው። የዛሬው የኤርትራ ጣሂር ዘንድሮ ሊያስቸግር የቻለበት አብይ ምክንያት ባለፉት ዓመታት ከኢትዮጵያ ጋር ያካሄደው

የድንበር ጦርነት ላይ ከርሰ መሬት ውስጥ አለመግባቱ ነው። ያ ነገር ፖለቲከኛ ስላልሆንኩኝ ሳይገባኝ ይቀር ይሆን እንጂ፡ በአልጀርሱ ስምምነት ላይ ሰላም፣ ሰላም፤ ተብሎ የነተሎ ተሎ ቤት ግድግዳው ሰምበሌጥ ሆኖ ስለታየኝ፡ የዛሬው ጣሂር አገግሞ ሌላ ጣሂር ፈጥሮ አገራችን ኢትዮጵያን ችግር ውስጥ ለመጥመድ መሞከሩ እንደ እንቆቅልሽ ስለሆነብኝ ነው። እንዲህ ስል ግን ለሰላም ሲባል የማይፈነቀል ድንጋይ መኖር የለበትም ማለቴ እንዳልሆነ ልትገነዘቡልኝ ይገባል። ያም ሆነ ይህ አሁን ምን ይሻላል? በትግርኛ አንድ ምሳሌ አለ። ይኸውም "ናይ ዘሓለፈስ ሓለፈ፣ ናይ ዝመፅእ ይበኸ" የሚባል አባባል ቁልጭ ብሎ እየታየኝ ነው። ትግርኛ ለማያውቁ ትርጉሙ እነሆ፡ ያለፈውስ አለፈ፡ ለሚመጣው እናስብ ለማለት መሰለኝ። የዛሬውቹ ጣሂሮች በነተሎ ተሎ ቤት እንዳይታለፉ ለማስታወስ ነው። በሚቀጥሉት ዓመታትም ሆነ አስርት ዓመታት እነ ጣሂር አገግመው ለአንድ ቀንም ሆነ ለሁለት ቀን ሰላማችን አደፍርሰው ልማታችንና ዕድገታችን እንዳያቃውሱ ስለምሰጋ ምን ያህል እንደ ተወቀጡ ለብዙዎቻችን አሳሳቢ እየሆነ እንደሆነ ለማስታወስ እፈልጋለሁ። በተለይም የኤርትራው ጣሂር ወደ ካይሮ እንደ ውሃ ቀጂ በሚመላለስበት ወቅት፡ ግብፅም ምን ያህል ሰላማችንና እፎይታችን እንደሚያሰጋት ታሳቢ በማድረግ፡ ሌላ ጣሂር ደግሞ ካይሮ ላይ ለመፍጠር የጫጉላ ሽርሽር የተያዘ መስሎ ስለታየኝ ነው። ቅድም እንደጠቀስኩት "Politics is a dirty game" (ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው) እንደሚባለው ሁሉ አንዳንዴ ወዴት እንደሚያዘነብል በደንብ ስለማይገባኝ ነው። ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ መሆኑ በብዙዎች ቢነገርም ለአንባቢያን ማስረጃ እንዲሆን አንድ ምሳሌ ልጠቅስላችሁ። እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1993 ዓ/ም፡ አሜሪካ በሶማሊያ ምድር ሰላም ለማስፈን ሲባል ወታሃደሮቿን ወደ ሞቃዲሾ ላከች። የጅኦግራፊም ሆነ የአየር ጠባይ አለመሳካት በጦርነቱ በኩል ድል አልተቀዳጀችም። በዚሁ ሳቢያ ወታሃደሮቿ በመቃዲሾ ጎዳናዎች ታላቅ ችግር ገጠማቸው። ሂለኮፕተሯም ተከሰከሰ። የዚሁ ድርጊት ዋና ተዋናይ የነበሩት ከጥቂት ዓመታት በፊት በሞት ከዚህ ዓለም የተለዩት አቶ አይዲድ ነበሩ። በዚህ ምክንያት ልጃቸው ሁሴን አይዲድ የአሜሪካ ወታደሮች በሞቃዲሾ ጎዳናዎች ያሸነፈ ልጅ ስለተባለ በሱማሌዎች ዘንድ በጀግንነት ሲጠራ የነበረ ሰው ነው። ዘንድሮ ደግሞ የሶማሊያ የሽግግር መንግስት የአገር ጉዳይ ሚ/ር ሆኖ ስለተሾመ፣ ሰሞኑን የአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖች ደቡብ ሶማሊያን መደብደባቸው ትክክለኛ እርምጃ ነው ብሎ ቃል ሲያቀብል የዓለም ህዝቦች

በሁሴን ውሳኔ ተደነቁ። ወንድሞቼ፡ እንዲህ ነው እንግዲህ ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው የተባለው። ስለሆነም፡ ነብዪዎች አይደለንምና ነገ በፖለቲካው መስክ የሚከሰተው ጉዳይ ስለማናውቅ፡ የአገራችንና የወገኖቻችን የጋራ ጥቅም የሚፃረሩና የነገው ሰላማችን ለማደፍረስ እንቅልፍ የማይወስዳቸው ዲክተተሮችና አጫፋሪዎቻቸው ሳይቀሩ ተደቁሰው ግብኣተ-መሬት ሳይዘልቁ፣ ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን ከሶማሊያ መውጣት እንደሌለበት ለሚመለከተው እንዲደርስ ነው እቺ ሚጢጢ ፅሑፍ ለመክተብ የበቃሁት።

መልእክታችሁ በሚከተለው ኢሜል ይደርሰኛልና ክተቡልኝ።

besrattshore@yahoo.com

የነገ ሰው ይበለን!!